ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በጣም በቅርቡ ወደ ምድር ተመልሶ ሊመጣ ነው። ከ2000 ዓመታት በፊት በዚህ በምድር ላይ ሳለ ያደረገው(የገባው) የተስፋ ቃል ይህ ነው (ዮሐ. 14:1-3)። እርሱ በእርግጠኝነት እንደሚመለስ እንዴት በእርግጥ የእውነት ማወቅ እንችላለን? ራሱ ጌታ ኢየሱስ በመጨረሻው ዘመን (በፍጻሜ ሰዓታት) ስለሚሆኑት(ይሆናሉ ስላላቸው) ነገሮች የተናገረውን ትንቢቶች(ትንበያዎች) እባካችሁ አንብቡ። እነዚህን ቃላት በጥንቃቄ ማንበብና አሁን በዓለም ላይ እየሆኑ ካሉት ድርጊቶች(ሁኔታዎች) ጋር ቃላቱን ማነጻጸር ጌታ ኢየሱስ በእኛ የሕይወት ዘመን የእውነት ተመልሶ እንደሚመጣ ያረጋግጣል።

## 1 የመቅደስ መፍረስ

ኢየሱስም ከመቅደስ ወጥቶ ሄደ፥ ደቀ መዛሙርቱም የመቅደሱን ግንቦች ሊያሳዩት ቀረቡ። እርሱ ግን መልሶ። ይህን ሁሉ ታያላችሁን? እውነት እላችኋለሁ፥ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ በዚህ አይቀርም አላቸው። (ማቴ 24:1-2፤ ማር 13:1-2፤ ሉቃ 21:5-6)። ይህ በ70 ዓ.ም የእውነት ተፈጽሞአል።

## 2 የመምጣቱ ምልክት

እርሱም በደብረ ዘይት ተቀምጦ ሳለ፥ ደቀ መዛሙርቱ ለብቻቸው ወደ እርሱ ቀርበው። ንገረን፥ ይህ መቼ ይሆናል? የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክቱስ ምንድር ነው? አሉት። (ማቴ 24:3፤ ማር 13:3-4፤ ሉቃ 21:7)

## 3 አሳቾች ይነሣሉ

ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው። ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ። ብዙዎች። እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና፤ ብዙዎችንም ያስታሉ። ስለዚህ ተከትላችኋቸው አትሂዱ። (ማቴ 24:4-5፤ ማር 13:5-6፤ ሉቃ 21:8)

## 4 ጦርነቶችና የጦርነቶች ወሬ

ጦርንም የጦርንም ወሬ ትሰሙ ዘንድ አላችሁ፤ ይህ ሊሆን ግድ ነውና ተጠበቁ፥ አትደንግጡ፤ ዳሩ ግን መጨረሻው ገና ነው። (ማቴ 24:6፤ ማር 13:7፤ ሉቃ 21:9)

## 5 የሕዝብ በሕዝብ ላይ ጦርነቶች | የመሬት መንቀጥቀጦች | ረሃቦች | በሽታዎች

ሕዝብ በሕዝብ ላይ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣልና፥ ራብም ቸነፈርም የምድርም መናወጥ በልዩ ልዩ ስፍራ ይሆናል፤ (ማቴ 24:7፤ ማር 13:8፤ ሉቃ 21:10-11)

**6** እነዚህም ሁሉ የምጥ ጣር መጀመሪያ ናቸው። (ማቴ 24:8፤ ማር 13:8)

## 7 ሥቃይ ለክርስቲያኖች

እናንተ ግን ለራሳችሁ ተጠንቀቁ፤ ከዚህም ሁሉ በፊት እጃቸውን በላያችሁ ይጭናሉ ያሳድዱአችሁማል፤ ወደ ሸንጎ አሳልፈው ይሰጡአችኋል በምኵራብም ትገረፋላችሁ፤ ወደ ወኅኒ አሳልፈው ይሰጡአችኋል፥ ለመከራ አሳልፈው ይሰጡአችኋል ይገድሉአችሁማል። ስለ ስሜም ወደ ነገሥታትና ወደ ገዥዎችም ይወስዱአችኋል። ይህም ለምስክርነት ይሆንላችኋል። (ማቴ 24:9፤ ማር 13:9፤ ሉቃ 21:12-13)

**8** ሲጐትቱአችሁና አሳልፈው ሲሰጡአችሁም ምን እንድትናገሩ አስቀድማችሁ አትጨነቁ፥ ስለዚህ እንዴት እንድትመልሱ አስቀድማችሁ እንዳታስቡ በልባችሁ አኑሩት፤ ዳሩ ግን በዚያች ሰዓት የሚሰጣችሁን ተናገሩ፤ የሚነግረው መንፈስ ቅዱስ ነው እንጂ እናንተ አይደላችሁምና። ወደረኞቻችሁ ሁሉ ሊቃወሙና ሊከራከሩ የማይችሉትን አፍና ጥበብ እሰጣችኋለሁና።

## 9 በቤተሰዎች ውስጥ ክህደት

በዚያን ጊዜም ብዙዎች ይሰናከላሉ። ወንድምም ወንድሙን አባትም ልጁን ለሞት አሳልፎ ይሰጣል፥ ዘመዶችም ወዳጆችም አሳልፈው ይሰጡአችኋል፥ ልጆችም በወላጆቻቸው ላይ ይነሣሉ። ይገድሉአቸውማል፤ በሁሉም ስለ ስሜ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ። ከራሳችሁም አንዲት ጠጕር ስንኳ አትጠፋም፤ በመታገሣችሁም ነፍሳችሁን ታገኛላችሁ። (ማቴ 24:9-10፤ ማር 13:12-13፤ ሉቃ 21:16-19)

## 10 ፍቅር ትቀዘቅዛለች

ከዓመፃም ብዛት የተነሣ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች። እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል። (ማቴ 24:12-13)

**11** ለአሕዛብም ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፥ በዚያን ጊዜም (ከዚያም) መጨረሻው ይመጣል። (ማቴ 24:14፤ ማር 13:10)

## 12 የጥፋት ርኩሰት በኢየሩሳሌም

ኢየሩሳሌም ግን በጭፍራ ተከባ ስታዩ በዚያን ጊዜ ጥፋትዋ እንደ ቀረበ እወቁ። (ሉቃ 21:20)። እንግዲህ በነቢዩ በዳንኤል የተባለውን የጥፋትን ርኩሰት በተቀደሰችው ስፍራ ቆሞ ስታዩ፥ አንባቢው ያስተውል፥ በዚያን ጊዜ በይሁዳ ያሉ ወደ ተራሮች ይሽሹ፥ በመካከልዋም ያሉ ከእርስዋ ፈቀቅ ይበሉ፥ በገጠር ያሉም ወደ እርስዋ አይግቡ። በሰገነትም ያለ ወደ ቤት አይውረድ ከቤቱም አንዳች ይወስድ ዘንድ አይግባ፥ በእርሻም ያለ ልብሱን ይወስድ ዘንድ ወደ ኋላው አይመለስ። (ማቴ 24:15-18፤ ማር 13:14-16፤ ሉቃ 17:31፤ 21:21)። በዚያን ወራትም ለርጉዞችና ለሚያጠቡ ወዮላቸው!። ነገር ግን ሽሽታችሁ በክረምት ወይም በሰንበት እንዳይሆን ጸልዩ፤ (ማቴ 24:19-20፤ ማር 13:17-18፤ ሉቃ 21:23)። በሰይፍ ስለትም ይወድቃሉ፤ ወደ አሕዛብ ሁሉም ይማረካሉ፤ የአሕዛብም ዘመን እስኪፈጸም ድረስ ኢየሩሳሌም በአሕዛብ የተረገጠች ትሆናለች። (ሉቃ 21:24)

## 13 የያዕቆብ መከራ ዘመን (ኤርም 30:6-7)

በዚያን ወራት እግዚአብሔር ከፈጠረው ከፍጥረት መጀመሪያ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ያልሆነ ደግሞም የማይሆን የመከራ ዓይነት በዚህ ሕዝብ ላይ ይሆናልና። ጌታስ ወራቶቹን ባያሳጥር፥ ሥጋ የለበሰ ሁሉ ባልዳነም፤ ነገር ግን ስለ መረጣቸው ምርጦች ወራቶቹን አሳጠረ። (ማቴ 24:21-22፤ ማር 13:19-20፤ ሉቃ 21:23)። የተጻፈው ሁሉ እንዲፈጸም ይህ የበቀል ጊዜ ነውና። (ሉቃ 21:22)

## 14 ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት

በዚያን ጊዜም ማንም። እነሆ፥ ክርስቶስ ከዚህ አለ፥ ወይም። እነሆ፥ ከዚያ አለ! ቢላችሁ አትመኑ፤ ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፥ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ። እናንተ ግን ተጠንቀቁ፤ እነሆ፥ አስቀድሜ ሁሉን ነገርኋችሁ። (ማቴ 24:23-24፤ ማር 13:21-23)። እንግዲህ። እነሆ፥ በበረሀ ነው! ቢሉአችሁ፥ አትውጡ፤ እነሆ፥ በእልፍኝ ነው! ቢሉአችሁ፥ አትመኑ፤ መብረቅ ከምሥራቅ ወጥቶ እስከ ምዕራብ እንደሚታይ፥ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናልና፤ (ማቴ 24:26-27፤ ሉቃ 17:23-24)።

## 15 ምልክቶች በሰማያት

ከዚያች ወራትም መከራ በኋላ ወዲያው ፀሐይ ይጨልማል፥ ጨረቃም ብርሃንዋን አትሰጥም፥ ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ፥ የሰማያትም ኃይላት ይናወጣሉ። (ማቴ 24:29፤ ማር 13:24-25፤ ሉቃ 21:25)። በፀሐይና በጨረቃም በከዋክብትም ምልክት ይሆናል፤ በምድር ላይም አሕዛብ ከባሕሩና ከሞገዱም ድምፅ የተነሣ እያመነቱ ይጨነቃሉ፤ ሰዎችም ከፍርሃትና በዓለም የሚመጣበትን ከመጠበቅ የተነሣ ይደክማሉ፤ የሰማያት ኃይላት ይናወጣሉና። (ሉቃ 21:25-26)።

**16** በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል፥ በዚያን ጊዜም የምድር ወገኖች ሁሉ ዋይ ዋይ ይላሉ፥ የሰው ልጅንም በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል፤ መላእክቱንም ከታላቅ መለከት ድምፅ ጋር ይልካቸዋል፥ ከሰማያትም ዳርቻ እስከ ዳርቻው ከአራቱ ነፋሳት ለእርሱ የተመረጡትን ይሰበስባሉ። (ማቴ 24:30-31፤ ማር 13:26-27፤ ሉቃ 21:27)።



17 ይህም ሊሆን ሲጀምር ቤዛችሁ ቀርቦአልና አሻቅባችሁ ራሳችሁን አንሡ።

18 ምሳሌንም ነገራቸው እንዲህ ሲል። በለስንና ዛፎችን ሁሉ እዩ፤ ሲያቈጠቍጡ ተመልክታችሁ በጋ አሁን እንደ ቀረበ ራሳችሁ ታውቃላችሁ። እንዲሁ ደግሞ እናንተ ይህ ሁሉ መሆኑን ስታዩ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ ቀረበች እወቁ፥ በደጅ እንደ ሆነ እወቁ። (ማቴ 24:32-33፤ ማር 13:28-29፤ ሉቃ 21:29-31)። ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአባት ብቻ በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን የሚያውቅ የለም። (ማቴ 24:36፤ ማር 13:32)።

19 የኖኅ ዘመን እንደ ነበረ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናልና። በዚያች ወራት ከጥፋት ውኃ በፊት፥ ኖኅ ወደ መርከብ እስከገባበት ቀን ድረስ፥ ሲበሉና ሲጠጡ ሲያገቡና ሲጋቡም እንደ ነበሩ፥ የጥፋት ውኃም መጥቶ ሁሉን እስከ ወሰደ(አጠፋ) ድረስ እንዳላወቁ፥ የሰው ልጅ መምጣት ደግሞ እንዲሁ ይሆናል። (ማቴ 24:37-39፤ ሉቃ 17:26-27)።

20 እንዲሁ በሎጥ ዘመን እንደ ሆነ፤ ይበሉ ይጠጡም ይገዙም ይሸጡም ይተክሉም ቤትም ይሠሩ ነበር፤ ሎጥ ከሰዶም በወጣበት ቀን ግን ከሰማይ እሳትና ዲን ዘነበ ሁሉንም አጠፋ። የሰው ልጅ በሚገለጥበት ቀን እንዲሁ ይሆናል። (ሉቃ 17:28-30)።

21 የሎጥን ሚስት አስቡአት። ነፍሱን ሊያድን የሚፈልግ ሁሉ ያጠፋታል፥ ነፍሱንም የሚያጠፋ ሁሉ በሕይወት ይጠብቃታል። (ሉቃ 17:32-33)።

22 እላችኋለሁ፥ በዚያች ሌሊት ሁለት ሰዎች በአንድ አልጋ ይሆናሉ፤ አንዱ ይወሰዳል ሁለተኛውም ይቀራል። ሁለት ሴቶች በአንድ ወፍጮ ይፈጫሉ፤ አንዲቱ ትወሰዳለች ሁለተኛይቱም ትቀራለች። ሁለት ሰዎች በእርሻ ይሆናሉ፤ አንዱ ይወሰዳል ሁለተኛውም ይቀራል። (ማቴ 24:40-41፤ ሉቃ 17:34-36)። መልሰውም። "ጌታ ሆይ፥ ወዴት ነው?" አሉት። እርሱም። "ሥጋ ወዳለበት በዚያ አሞራዎች ይሰበሰባሉ" አላቸው። (ማቴ 24:28፤ ሉቃ 17:37)።

23 የምትተጉ እና የምትጸልዩ ሁኑ
ቤቱን ትቶ ወደ ሌላ አገር እንደ ሄደ ሰው ነው፥ ለባሮቹም ሥልጣን ለእያንዳንዱም ሥራውን ሰጥቶ በረኛውን እንዲተጋ አዘዘ። እንግዲህ በማታ ቢሆን ወይም በእኩለ ሌሊት ወይም ዶሮ ሲጮኽ ወይም በማለዳ ቢሆን ባለቤቱ መቼ እንዲመጣ አታውቁምና ድንገት መጥቶ ተኝታችሁ እንዳያገኛችሁ ስለዚህ ትጉ። (ማር 13:34-36)።

24 ያን ግን እወቁ፤ ባለቤት ከሌሊቱ በየትኛው ክፍል ሌባ እንዲመጣ ቢያውቅ ኖሮ፥ በነቃ ቤቱም ሊቈፈር ባልተወም ነበር። ስለዚህ እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ፥ የሰው ልጅ በማታስቡበት ሰዓት ይመጣልና። (ማቴ 24:43-44)።

25 ነገር ግን ልባችሁ በመጠጥ ብዛትና በስካር ስለ ትዳርም በማሰብ እንዳይከብድ፥ ያ ቀንም በድንገት እንዳይመጣባችሁ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። ጊዜው መቼ እንዲሆን አታውቁምና ተጠንቀቁ፤ ትጉ፤ ጸልዩም። በምድር ሁሉ ላይ በሚቀመጡ ሁሉ እንደ ወጥመድ ይደርስባቸዋልና። (ማር 13:33፤ ሉቃ 21:34-35)።

26 እንግዲህ ሊመጣ ካለው ከዚህ ሁሉ ለማምለጥ፥ በሰው ልጅም ፊት ለመቆም እንድትችሉ ስትጸልዩ ሁል ጊዜ ትጉ። (ሉቃ 21:36)።

27 እውነት እላችኋለሁ፥ ይህ ሁሉ እስኪሆን ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍም። ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን አያልፍም። (ማቴዎስ 24:34-35፤ ማርቆስ 13:30-31፤ ሉቃስ 21:32-33)።


Watch online through www.angeltv.org

ANGEL TV
Satellite :INTELSAT20 @68.5°East
Band :Ku
Downlink Frequency :12.522GHz
SymbolRate :27500Msps
FEC :3/4
Modulation :MPEG2
Polarization :Vertical


Local Contact Address

ታላቁ ንጉሥ - ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ
በከበረ ውብ ዙፋኑ ላይ ተቀምጦ
በቅዱሳን መላእክቶቹና ቅዱሳኑ ታጅቦ
በታላቅ ኃይልና ክብር
በጣም በቅርቡ
በድጋሜ እየመጣ ነው።

የፍርዱ ሰዓት ደርሶአልና
እግዚአብሔርን ፍሩ
ክብርንም ስጡት፤
ሰማይንና ምድርንም
ባሕርንም
የውኃንም ምንጮች
ለሠራው ስገዱለት

(ራእይ 14:7)

ሰዓት ከእንግዲህ አይዘገይም!
መንግሥተ ሰማይ ቀርባለች አሁን። ንስሐ ግቡ እና በዚህ ወንጌል እመኑ።
ጌታ አምላካችሁን ለመገናኘት ተዘጋጁ!



# የእግዚአብሔር መንግሥት ወንጌል

አማርኛ | ETHIOPIAN